የሰ/መ/ቁ. 236987

ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች:-

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኘ

**አመልካች፡** ወ/ሮ አይናለም ሄና ፊቃዱ

**ተጠሪ፡** ወ/ሮ ረምላ ሳቢር

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የዉርስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች ባቀረቡት ክስ የሟች ወላጅ አባቴ የዉርስ ንብረት እንዲጣራ ዳኝነት ጠይቄ በመ/ቁጥር 43370 ላይ የዉርስ ሀብት ተጣርቶ የተወሰነ ቢሆንም፣ በጉራጌ ዞን በቡታጅራ ከተማ እሪንዛፍ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 ክልል ዉስጥ ልዩ ስሙ ሀቱ ተብሎ በሚጠራዉ መንደር ዉስጥ አዋሳኙ የተጠቀሰዉን ሟች አባቴ ለሰርግ መናፈሻ አገልግሎት እንዲዉል ይዞት ቤትና የተለያዩ አትክልቶች ያሉበት ስፋቱ በግምት 8000 ካ/ሜትር ይዞታ ተጠሪ በመደበቋ ሳይጣራ የታለፈ መሆኑን ጠቅሰዉ በዉርስ አጣሪ ይጣራልኝ በሚል የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸዉ የመጀመሪያ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር ያቀረቡ ሲሆን፣ በመጀመሪያ መቃወሚያነት ያቀረቡት መልስ ይዘትም ጉዳዩ በመ/ቁጥር 43370 ላይ ዉሳኔ ያገኘ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ የሚል ነዉ፡፡

ፍርድ ቤቱም በቀረበዉ የመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት እንዲጣራ በአመልካች እና በሌሎችም ወራሾች በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የዉርስ ንብረት ተጣርቶ ጥቅምት 19 ቀን 2007 ዓ.ም የዉርስ አጣሪ ሪፖርት የቀረበ መሆኑን፣ በወቅቱም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ይዞታ የሟች መሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል በዉርስ አጣሪ ሪፖርቱ የተገለጸ ሲሆን ሪፖርቱም ጉድለት የለበትም ተብሎ በፍርድ ቤት የጸደቀ ሲሆን በይግባኝ አለመሻሩን ጠቅሶ አመልካች ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በማለት በብይን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የይግባኝ መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች ህዳር 03 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከዚህ በፊት በመ/ቁጥር 43370 ላይ የጸደቀዉ የዉርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ዉርስ አጣሪዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በተመለከተ የዉርስ አጣሪዉ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉን ገልፆ ባቀረበዉ ሪፖርት ላይ ፍርድ ቤቱ ምንም አስተያየት ሳይሰጥበት ያለፈ ሲሆን፣ በሌላ በኩል አንድ ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ ነዉ ለማለት የሚቻለዉ በማስረጃ ተጣርቶ ዉሳኔ የተሰጠበት መሆን እንዳለበት እና በተያዘዉ ጉዳይ በዉርስ ማጣራት ወቅት ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም
Abrham Yohanes

ቤቱ አጣርቶ ዉድቅ ባላደረገበት ሁኔታ ዉሳኔ አርፎበታል ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ በሌለበት ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ታርሞ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉም በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ የዉርስ አጣሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በተመለከተ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ያለፈዉን የመጨረሻ ዉሳኔ እንደተሰጠበት ተደርጎ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በሚል ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ፣ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት የካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በዝርዝር በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሟች የዉርስ ሀብት ተጣርቶ ባለበት ሁኔታ አመልካች ያቀረቡት የዳግም የዉርስ ይጣራልኝ ዳኝነት ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የሟች አቶ ፍቃዱ ሰሴሮ የዉርስ ሀብት በዉርስ አጣሪ ተጣርቶ ሪፖርቱም ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ የጸደቀ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች ላቀረቡት የዉርስ ይጣራልኝ አቤቱታ መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የሚገኝበት ቦታ ወራሾች ባለማወቃቸዉ እና ተጠሪም የለም ብለዉ በመደበቃቸዉ ዉርስ ሲጣራ በነበረበት ወቅት ሳይጣራ ታልፏል የሚል ይዘት ያለዉ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

በመሠረቱ ስለ ዉርስ የሚደደነግገዉ የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ ሟች እንደሞተ የውርስ ሀብት የማጣራት ስራ ተከናዉኖ ለወራሾች የሚተላለፈው የጠራ ሀብት ከተለየ በኋላ የውርስ ክፍፍል እንደሚፈፀም ያዛል፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 942 *ዉርስ እስከተጣራ ድረስ እንደ ተለየ ንብረት ሆኖ ይቆጠራል (so long as a succession has not been liquidated, it shall constitute a distinct estates)* በሚል የሚደነግግ ሲሆን፣ ይሄም የዉርስ ማጣራት ሥርዓትን የሚገዛ መሪ ደንብ ነዉ፡፡ በዚህ መሪ ደንብ መሠረት የዉርስ ንብረት ከመጣራቱ በፊት የዉርስ ንብረት እንደ አንድ የተለየ የማይከፋፈል ንብረት ሆኖ ስለሚቆጠር የሟች ወራሾች እና የዉርስ ንብረቶች መለየትና መወሰን እንዲሁም ዉርስ ዕዳዎችን የመለየትና የመክፈል ተግባር እስኪከናዉን ድረስ የዉርስ ሀብቱ ከወራሾች ንብረት ጋር ሳይቀላቀል ይቆያል፡፡ ከዉርስ ሐብት ላይ ገንዘብ ለመጠየቅ መብት ያላቸዉ ሰዎች ማለትም የሟች አበዳሪዎች እና የፍርድ ባለመብቶች ለገንዘባቸዉ ዋስትናና መያዥያ የሚሆናቸዉ ይሄዉ በመጣራት ላይ ያለዉ የዉርስ ንብረት ነዉ፡፡ በመሆኑም የሟች ዉርስ በመጣራት ላይ እያለ ከሟች ወራሾች ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎች በወራሾች የግል ንብረት ላይ አንዳችም ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም፡፡ ከሟች ዉርስ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ያላቸዉ መብት የሟችን የዉርስ ንብረት መከታተል ብቻ ነዉ፡፡ የሟች የዉርስ ሀብት ድርሻም የሚታወቀዉ የሟች ዉርስ ከተጣራ ብቻ ነዉ፡፡ ዉርስ እንዲጣራ የሚደረገዉም በዚህ ምክንያት ነዉ፡፡

በዚህም መሠረት የፍትሐብሔር ህጉ ስለ ዉርስ ማጣራት በሚደነግገዉ ክፍል ዉርስ ማጣራት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጉም በመስጠት የሚጀምር ሲሆን፣ የዉርስ አጣሪ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ እንዲሁም በሂደቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በተለያዩ አንቀፆቹ ይደነግጋል፡፡


Abrham Yohanes

በፍትሐብሔር ህጉ እንደተመለከተዉ ዉርስ ማጣራት የሟች ወራሾች እነ ማን እንደሆኑ አጣርቶ መወሰን፣ የዉርስ ሀብት ምን መሆኑን መወሰን፣ ሌሎች ሰዎች ከሟች የተበደሩትን ገንዘብ መሰብሰብና በሟች ዉርስ ላይ ሊከፍላቸዉ የሚገቡ አስገዳጅ የሆኑ እዳዎችን አጣርቶ መክፈል እና ሟች በኑዛዜ ስጦታ ያደረገላቸዉ ሰዎች የተሰጣቸዉን መክፈል ስለመሆኑ የህጉ አንቀጽ 944 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዉርስ አጣሪዉ የሚከናወኑ ተግባራትንም ስንመለከት ሟች ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻ ዉርሱ የሚደርሳቸዉ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣ የዉርስ ሀብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸዉ የደረሰዉን የዉርስ ዕዳዎች መክፈል፣ ሟች በኑዛዜ ያደረጋቸዉን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜዉን ቃል ለመፈጸም ማናቸዉም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን በማድረግ ተገቢዉን ሁሉ ካደረገ በኋላ በመጨረሻም የዉርስ ማጣራት ስራዉ የሚዘጋ (closure of the liquidation) ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 956 እና 1052 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ ሁሉ ሂደት አልፎ ዉርስ ተጣርቶ የተዘጋ እንደሆነ የዉርስ ማጣራት የታለመለትን ዓላማ እንዳሳካ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም በዉርስ ማጣራት ሂደት ግድፈት አይኖርም ወይም መጣራት የሚገባቸዉ ሁሉ ተጣርተዋል ወይም በሂደቱ የወራሾች ወይም የሟች ገንዘብ ጠያቂዎች መብት አይነካም ማለት አይደለም፡፡ የዉርስ ማጣራት ሂደቱ በአግባቡ ባለመከናወኑ ወይም በሌላ ምክንያት መካተት የሚገባቸዉ ንብረቶች ሳይካተቱ በመቅረታቸዉ ወይም መካተት ሳይገባቸዉ በመካተታቸዉ ወይም ወራሽ የሆነ ሰዉ ስሙ ባለመካተቱ ምክንያት ወይም ከዉርስ ሀብት ገንዘብ ሊከፈለዉ የሚገባዉ የሟች ባለገንዘብ ሳይከፈለዉ ሊቀር የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በዚህም ምክንያት በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ጉዳት ደርሶብኛል ወይም መብቴ ተነክቷል ወይም ወራሽነቴ ይረጋገጥልኝ የሚል ሰዉ መብቱን ሊያስከብር የሚችልበት ሥርዓት ሊኖር ግድ ይላል፡፡ ይህን ሁሉ ከግምት ዉስጥ በማስገባትም የፍትሐብሔር ህጉ ስለ ዉርስ በሚደነግገዉ ክፍሉ ከዉርስ ጋር በተያያዘ መብት ያለዉ ወገን ለፍርድ ቤት አቤቱታ/ክስ አቅርቦ መብቱን ሊያስከብር የሚችልባቸዉን ሥርዓቶች ይደነግጋል፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህልም፣ ወራሽ መሆኑንና ከዉርስ ሀብቱ የሚደርሰዉን የድርሻ መጠን የሚያመለክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት ፍርድ ቤት እንዲሰጠዉ መጠየቅ እንደሚቻል እና ፍርድ ቤቱም ከሳሹ ያቀረበዉን ማስረጃ ጨምሮ ተገቢዉን ማጣሪያ በማድረግ አስፈላጊ ከሆነም ዋስትና እንዲቀርብ በማድረግ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ፣ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ሰዉም በማስረጃዉ ላይ በተገለጸዉ መሠረት ወራሽ ነዉ ተብሎ እንደሚገመት፤ በፍርድ ቤት የተሰጠዉ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ወራሽ በሆነ ሰዉ ክስ ማቅረብ እንደሚቻል እና ፍርድ ቤቱም የወራሽነት የምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ሰዉ ወራሽ አለመሆኑን ካረጋገጠ እንደ ነገሩ ሁኔታ የተሰጠዉን የወራሽነት የምስክር ወረቀት በመሰረዝ ወይም እንዲመለስ ወይም ተከሳሹ እንዳይገለገልበት ዉሳኔ መስጠት እንደሚችል፤ የወራሽነት መብት በሌለዉ ሰዉ የተያዘ ንብረት እንዲመለስ እዉነተኛ ወራሽ ክስ ማቅረብ እንደሚችል፤ የዉርስ ማጣራት ሂደቱ ተከናዉኖ የዉርስ ክፍያ ከተደረገ በኋላ በዉርስ ንብረት ዉስጥ ገብተዉ የሚቆጠሩ አዲስ ሀብቶች የተገኙ እንደሆነ በተገኙት አዲስ ንብረቶች መጠን ክፍያ በድጋሚ እንዲደረግ መጠየቅ እንደሚቻል፣ የአንዳንድ ንብረቶች ዋጋ በተሳሳተ ሁኔታ የተገመተ መሆኑ ከታወቀም የዉርስ ክፍያ ሥርዓቱ እንዲቃና መጠየቅ እንደሚቻል እንዲሁም የዉርስ ሀብት ከተከፋፈለ በኋላ የሚመጣ ገንዘብ ጠያቂ ካለ ወራሾች በደረሳቸዉ ድርሻ ልክ ዕዳዉን እንዲከፍሉ መጠየቅ እንደሚቻል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 996-999፣ 1003፣ 1005 እና 1010 ላይ የተመለከቱትን ማየት ይቻላል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም
Abrham Yohanes

ከላይ በዝርዝር ያየናቸዉ ሃሳቦች በአጠቃላይ የሚያሳዩን የዉርስ ማጣራት ስራ የሟች ንብረቶችን፣ የሟች ወራሾችን፣ የሟች ኑዛዜ ተጠቃሚዎችን እና የሟች ባለገንዘቦችን ለይቶ ከዉርስ ሀብት ሊከፈሉ የሚገባቸዉ ዕዳዎች ከፍሎ በመጨረሻም ለወራሾች የሚተላለፈዉን ሀብት መለየት ሲሆን፤ በወራሾች በእራሳቸዉ ወይም በፍርድ ቤት በሚሾም የዉርስ አጣሪ የማጣራት ስራዉ ተከናዉኖ የተዘጋ እንደሆነ በማጣራቱ ሂደት በተፈጸመ ግድፈት ወይም በሌላ ምክንያት መብቱ የተነካበት ሰዉ ካለ በሌላ አግባብ መብቱን ማስከበር የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡ በሌላ አነጋገር ዉርስ ማጣራት የወራሽነት መብትን ማረጋገጥ ከሚቻልባቸዉ መንገዶች አንዱ እንጂ ብቸኛዉ መንገድ አለመሆኑን ነዉ፡፡ ይልቁንም፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ የውርስ ማጣራት ዋና ዓላማ ባለቤቱ በመሞቱ ምክንያት በቤተሰቦቹ (ወራሾቹ) ዙሪያ በሚፈጠር ያለመረጋጋትና የአስተዳደር ችግር ወይም በሌላ ምክንያት የውርስ ሀብት በየአቅጣጫው እንዳይባክንና የሟች ሀብት በአግባቡ ተጠብቆ በሕጉ ለሚገባቸው ወራሾች እንዲተላለፍላቸው ለማድረግ፤ እንዲሁም የሟች ገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ እንጂ፣ ወራሾች ከሟች ንብረት ጋር በተያያዘ ያላቸዉን መብት ብቻ ለመጠበቅ አይደለም፡፡ የዉርስ ማጣራት ስራ ተጠናቆ የማጣራት ሂደቱ መዘጋቱ ከታወቀ የሟች ንብረቶች፣ የሟች ወራሾች፣ የሟች የኑዛዜ ተጠቃሚዎች እንዲሁም የሟች ባለገንዘቦች ተለይተዉ ታዉቀዉ ከዉርስ ሀብቱ የሟች ባለ ገንዘቦች እና የኑዛዜ/ስጦታ ተጠቃሚዎች ካሉ ከዉርስ ንብረቱ ተከፍሎ እንደተጠናቀቀ የሚገመት ከመሆኑ አንፃር በድጋሚ የዉርስ ይጣራልኝ/ን አቤቱታ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚገባበት ህጋዊ ምክንያት የለም፤ ፍርድ ቤትም ዳኝነቱን ሊቀበለዉ አይገባም፡፡ በዉርስ ማጣራት ወቅት ያልቀረበ ወራሽ መቅረቡ፣ በወቅቱ ያልተገኘ ንብረት መገኘቱ በወቅቱ ያልቀረበ የሟች ባለ ገንዘብ መቅረቡ ብቻዉን ዉርስ እንዲጣራ ጥያቄ ለማቅረብ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

በዉርስ አጣሪ ተጣርቶ የቀረበ የዉርስ ማጣራት ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቁ የማስረጃ ዋጋ ያለዉ ቢሆንም፣ እንደ ፍርድ ሊቆጠር እንደማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 18576 (ቅጽ 7 ላይ የታተመዉን ጨምሮ) በሌሎችም መዛግብት ላይ ገዥ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ የዉርስ አጣሪ ሪፖርትን ሲያጸድቅ አንድን አከራካሪ ጭብጥ ይዞ፣ አከራክሮ እና ማስረጃን ሰምቶ የፍርድ ዉጤት በሚኖረዉ መልኩ የወሰነዉ ካልሆነ በቀር፣ የዉርስ አጣሪ ያቀረበዉን ሪፓርት በማጽደቅ የሰጠዉ ዉሳኔ በሌላ ክርክር እና ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም የዉርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቁም ከዉርስ ማጣራት ሂደት ጋር በተያያዘ ወይም በሌላ ምክንያት መብቴ ተነክቷል የሚል ሰዉ በሌላ አግባብ መብቱን እንዳያስከብር ምክንያት አይሆንም፡፡

በአጠቃላይ የዉርስ ማጣራት ስራ የተከናወነ መሆኑ ከታወቀ በዉርስ ማጣራቱ ሂደት መብቴ ተነክቷል ወይም በሌላ በማንኛቸዉም ምክንያት ከወራሽነት መብት ጋር በተያያዘ መብቴ ተነክቷል የሚል ሰዉ ዳኝነት ከፍሎ በሚመለከተዉ አካል ላይ በህግ አግባብ ክስ አቅርቦ መብቱን ማስከበር ከሚችል በስተቀር በድጋሚ የዉርስ ይጣራልኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች የሟች አባታቸዉ ዉርስ ከዚህ በፊት በዉርስ አጣሪ ተጣርቶ ሪፖርቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቁን ሳይክዱ፣ የዉርስ ይጣራልኝ አቤቱታ በድጋሚ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ ዉርስ በሚጣራበት ወቅት የት እንደሚገኝ ባለመታወቁ እና ተጠሪም በወቅቱ መደበቃቸዉን በመግለጽ ነዉ፡፡ ይሁንና በወቅቱ ሳይታወቅ ቀርቷል አልተካተተም የሚሉ ከሆነ ምክንያቱን ጠቅሰዉ መብታቸዉን በሌላ አግባብ ማስከበር ከሚችሉ በቀር

በድጋሚ የሚች የዉርስ ሀብት እንዲጣራ ፍርድ ቤቱ የዉርስ አጣሪ እንዲሾምላቸዉ የጠየቁት ዳኝነት የዉርስ ሀብት ማጣራት አስፈላጊነት እና ዓላማን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ከመነሻዉም ዉድቅ ሊደረግ የሚገባዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም፣ ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ተቀብሎ ነገር ግን ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በማለት የሰጠዉን ብይን በማጽናት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 97057 ላይ ሚያዝያ 08 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር በመ/ቁጥር 282683 ላይ ነሐሴ 30 ቀን 2014 290314 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች መብታቸዉን ለማስከበር በህግ አግባብ የሚያቀርቡትን ክስ ይህ ዉሳኔ አይከለክልም፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ገ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም
Abrham Yohanes